“ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና….” 1ኛ ተሰሎንቄ 1:5

2017

# በ 1ኛው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች መሰረት የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ደብተር

ስም፡……………………………………………………………………………………………

የመድኃኒዓለም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን - ሰይንት-ሉዊስ
የትምህርት ክፍል ያዘጋጀው

-----------------------------------------------------------------------------------

# 1. መግቢያ

## የተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያን አጭር የአመሰራረት ታሪክ

የሐዋርያው ጳውሎስ 2ኛው የሚስዮናዊነት ጉዞ መነሻ የአንጾኪያ ከተማ ነበረች። ለረጅም ቀናት ከበርናባስ ጋር ሆነው የጌታን ቃል እያስተማሩ በነበሩበት ጊዜ: ጳውሎስ በልቡ እንድ ሃሳብ መጣበት። እርሱም በመጀመርያው የሚስዮናዊነት ጉዞአቸው የመሰረቷቸውን ማኅበራት ተመልሶ ማየት የሚል ነበር። ስለዚህም በርናባስን “ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እንጐብኛቸው፥ እንዴት እንዳሉም እንወቅ አለው” (የሐዋርያት ሥራ 15:36)። ይህ በሐዋርያነት አገልግሎት የተጠሩ ሰዎች የሚያደርጉት የተለመደ መንፈሳዊ አሰራር ነው። ይህን ለማድረግ: ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ ይረዳኛል ብሎ የመረጠውን ሲላስን ይዞ መንገዱን ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራን አመራ። ጢሞቴዎስ እስከ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ድረስ ስሙ ሲጠራ ባናገኘውም: በመጀመርያው የጳውሎስና የበርናባስ የሚስዮናዊነት ጉዞ: ወደ ጌታ መጥቶ ይሆናል የሚል ትክክለኛ ግምት አለን። ይህም የምንልበት ምክንያት:

ለጢሞቴዎስ “በልስጥራንና በኢቆንዮን ያሉ ወንድሞች መሰከሩለት (የሐዋርያት ሥራ 16:2)” የሚል ቃል ስለምናነብ ነው።

ጳውሎስ: ሲላስና ጢሞቴዎስ ከደርቤንና ልስጥራን በመነሳት፣ በፍርግያና በገላትያ አድርገው ወደ እስያ ለመሄድና ወንጌልን ለማስፋፋት ሞከሩ። ሆኖም ግን መንፈስ ቅዱስ አልፈቀደላቸውም። እንደገናም ቢታንያ ወደሚባል አገር ለመሄድ ሲሞክሩ፣ አሁንም መንፈስ ቅዱስ ከለከላቸው። በመጨረሻ; ጢሮአዳ ወደሚባል አገር በወረዱ ጊዜ ግን፣ ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ መሄድ እንዳለባቸው የሚጠቁም አንድ ራእይ አየ። ራእዩንም ተከትለው: የመቄዶንያ ዋና ከተማ ወደ ሆነቸው ወደ ፊልጵስዩስ ደረሱ። በፊሊጲም ከተማ: በኤውሮጳ የመጀመሪያይቱን ቤተክርስቲያን: በሊድያ ቤት መሰረቱ። እንዲህ በማገልገል ላይ እያሉ ግን፣ በከተማይቱ ከሚኖሩ ከአንዳንድ ሰዎች እጅግ ከፍተኛ የሆነ ስደትና መከራ፣ ከዛም አልፎ እግልትና እስራት ደረሰባቸው። ለቤቱና ለልጆቹ ሁሌ የሚጠነቀቅ እግዚአብሔር ግን በሚያስደንቅ ተአምራት ከእስር ቤት አወጣቸውና ተመልሰው ወደ ሊድያ በመሄድ ተሰብስበው የነበሩትን የጌታ ሰዎች

አጽናንተው፡ ከተማይቱን ተሰናብተው: በአንፊጶልና በአጶሎንያ አልፈው: ወደ ተሰሎንቄ ከተማ ገቡ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከተማ የቆየው፡ ለ4 ሳምታት ያህል ነው። በነዚህ ጥቂት ሳምታት ውስጥ ግን: በአይሁድ ምኵራብ ገብቶ፡ እየሱስን በኀኃይል እየሰበከና እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ እያሳየ ቆየ። ይህንን ወንጌል የሰሙ ብዙዎች የከተማይቱ ሴቶችና እንዳንድ ግሪኮችም: ማመንና ከጳውሎስ ጋር መተባበር ጀመሩ። የእግዚአብሔር ስራ ሲሰራ ደስ የማይለው ጠላት ግን፡ አሁንም፡ የተወሰኑ ሰዎችን በቅንአትና በአድመኝነት አነሳስቶ፡ በነዚህ አዲስ አማኞች ላይ መከራ አመጡባቸው። ሌሎች የከተማይቱ ሰዎች ሰብስበውም፡ ከተማዋን አወኩ:: በአለቆች ፊትም እነ ጳውሎስንና እነዚህ አዲስ አማኞችን “የተቀበሉት ወንጌል አለምን የሚያውክ ነው” “ከቄሳር በላይ ነው የሚሉት ሌላ እየሱስ የሚባል ንጉስ አላቸው” ብለው ፖለቲካዊ ክስ አቀረቡባቸው። አንገላቱአቸውም:: በሐዋርያት ሥራ 17:10 እንደምናነበው: ጳውሎስና ሲላስ የተሰሎንቄን ከተማ በሌሊት እንደለቀቁ: ጢሞቴዎስ ግን ምናልባት ለጥጥቂት ቀናት እዛው እንደቀረ ይመስላል። ይህ የምንልበት ምክንያት፡ ምናልባት ከእነርሱ

ጋር ሄዶ ቢሆን ኖሮ፡ ስሙ አብሮአቸው ይጠራ ነበር ብለን ነው። ቆይቶ እንደደረሰባቸው ግን: በሐዋርያት ሥራ 17:14-15 ማንበብ እንችላለን። እንግዲህ በዚህ መልክ ነው የተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያን የተመሰረተችው። ጳውሎስም በጣም ከሚወዳቸው ወንድሞችና እህቶች ጋር ጊዜ ሳያሳልፍና የእግዚአብሔር ቃል በደንብ ሳይመግባቸው መለየት ነበረበት።

**2. የመልዕክቱ ዓላማ**

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያንና የምእመኖቿ ጉዳይ በጣም ያሳስበው እንደነበር፡ እንደገና ተመልሶም እነዚህ ወገኖች የነበሩበትን ሁኔታ ለማወቅና: እነርሱን ለማጽናናት ከልብ ይፈልግ እንደነበር ከመልዕክቱ መረዳት እንችላለን። ሆኖም ግን ፍላጎቱ ሊሳካለት አልቻለም። ከዚህም የተነሳ: ያሉበትን ሁኔታ ለማጥናትና: በእርሱ ቦታ ሆኖ ስለ እምነታቸው እንዲያጸናቸውና እንዲመክራቸው ብሎ ጢሞቴዎስን ይልከዋል። ጢሞቴዎስ ይዞለት የመጣው መልዕክት ግን ጳውሎስን ደስ አሰኝቶታል። አጽናንቶታልም። ምንም እንኳን ችግሩና መከራው ቢያይልባቸውም: የተሰሎንቄ ከተማ አማኞች በእምነታቸው እየበረቱ፡ በቁጥርም እየበዙ

እንደሆነ ይሰማል። ከዚህም የተነሳ፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህችን የመጀመሪያይቱን መልዕክቱን ለተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያን አማኞች:

1. **ለጌታ ስላሳዩት ታማኝነት እግዚአብሔርና እነርሱን ለማመስገን**
2. **በእምነታቸው እንዲጸኑና ጌታንና መንገዱን በማወቅ የበለጠ እንዲያድጉ እንዲያበረታታቸው**

በማሰብ ይጽፍላቸዋል።

አንደኛ ተሰሎንቄ: በዚህ ዘመን ለምንኖር አማኞችም ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶች የያዘ መልዕክት ነው። ህይወት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ እንዴት መኖር እንደምንችልና: የጌታን መምጣት ተስፋ በማድረግ እንዴት በእምነታችን መጽናትና በቅድስና መኖር እንደምንችል ያስተምረናል። ለዚህ እንዲረዳን ትምህርቱን እነዚህን 4 ነገሮች እያሰብን እናጠናዋለን።

1. የማጠናው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?
2. ስለ ሰው ባሕርይስ?

3. ከማጠናው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዛሬ እኔ ምን አዲስ ነገር እማራለሁ?
4. በተማርኩት የእግዚአብሔር ቃል መሰረት፡ በመንፈሳዊ ሕይወቴ ለማደግ ምን ማድረግ አለብኝ?

መልካም ጥናት!

## ጥናት ቁጥር 01

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 1:1-5

1 ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም
ለእናንተ ይሁን። 2-3 በጸሎታችን ጊዜ ስለ እናንተ ስናሳስብ፥
የእምነታችሁን ስራ የፍቅራችሁንም ድካም በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ
ያለውን የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ
እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን፤ 4
በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ተመረጣችሁ
አውቀናልና። 5 ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም
እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፤ በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ
እንዴት እንደ ነበርን ታውቃላችሁ።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 1:1-5) ስለ
   እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

# ጥናት ቁጥር 02

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 1:6-10

6 ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ፥ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፤ 7 ስለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምእመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው። 8 ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ አልተሰማምና፥ ነገር ግን ምንም እንድንናገር እስከማያስፈልግ ድረስ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆን እምነታችሁ በሁሉ ስፍራ ተወርቶአል። 9-10 እነርሱ ራሳቸው ወደ እናንተ መግባታችን እንዴት እንደነበረ ስለ እኛ ይናገራሉና፤ ለሕያውና ለእውነተኛ አምላክም ታገለግሉ ዘንድ፥ ከሙታንም ያስነሳውን ልጁን እርሱንም ኢየሱስን ከሚመጣው ቍጣ የሚያድነንን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ፥ ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር እንዴት ዘወር እንዳላችሁ ይናገራሉ።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 1:6-10) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

○ የእግዚአብሔርን ቃል ከብዙ መከራና ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር መቀበል ማለት ምን ማለት ነው?

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

4. የተሰሎንቄ ሰዎች: ጳውሎስ ሲላስና ጢሞቴዎስን እንደመሰሉ ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ቍጥር 6 ጽፏል። ዛሬ ሰዎች እርስዎን ቢመስሉ ጥሩ ነው ይላሉ? ለምን?

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

5. በ1ኛ ተሰሎንቄ 1:9-10 መሠረት: የአንድ ሰው የመዳን ምክንያት ምንድ ነው?

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

..............................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 03

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 2:1-12

1 ወንድሞች ሆይ፥ ራሳችሁ ወደ እናንተ መግባታችን ከንቱ እንዳልሆነ
ታውቃላችሁና።፤ 2 ነገር ግን እንደምታውቁት በፊልጵስዩስ አስቀድመን
መከራ ተቀብለን ተንገላትተንም፥ በብዙ ገድል የእግዚአብሔርን ወንጌል
ለእናንተ እንናገር ዘንድ በአምላካችን ደፈርን።3 ልመናችን ከስሕተት
ወይም ከርኵሰት ወይም ከተንኰል አልነበረምና፤ 4 ነገር ግን ወንጌልን
አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥
እንዲሁ እንናገራለን፥ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን
ደስ እንደምናሰኝ አይደለም። 5 እንደምታውቁ፥ እያቈላመጥን ከቶ
አልተናገርንም፥ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር እያመካኘን በመጐምጀት
አልሠራንም፤ 6 የክርስቶስም ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልንከብድባችሁ
ስንችል፥ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም። 7
ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትከባከብ፥ በመካከላችሁ የዋሆች
ሆንን፤ 8 እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል
ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን

ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና። 9 ወንድሞች ሆይ፥

ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ

እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ

ሰበክን።10 በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ

ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን፥ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች

ናችሁ፤ 11-12 ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር

እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም፥

አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሆንን ታውቃላችሁና።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 2:1-12) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

.........................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 2:1-12 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

3. በቍጥር 1-6 ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ወንጌል አልፎ የራሱንና ከእርሱ ጋር የሚያገለግሉትን ሰዎች ስም ለመጠበቅና ለመከላከል ሲሞክር እናነባለን። ይህ ለምን የሆነ ይመስልዎታል?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

4. ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቤተ-ክርስቲያን የሰጠውን አገልግሎት መጀመርያ በእናትነት (ቍጥር 7-8) ቀጥሎ በአባትነት (ቍጥር 9-12) ይመስለዋል።

   ○ በእናትነት የመሰለው ባሕርዩ የትኛውን ነው?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 04

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 2:13-16

13 ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ
በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ
እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ
ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።
14 እናንተ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በይሁዳ የሚኖሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ
ያሉትን የእግዚአብሔርን ማኅበሮች የምትመስሉ ሆናችኋልና፤ እነርሱ
ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ፥ እናንተ ደግሞ ያንን መከራ ከአገራችሁ
ሰዎች ተቀብላችኋልና። 15 እነዚያም ጌታን ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ
ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፥ እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፥ ሰዎችንም
ሁሉ ይቃወማሉ፥ 16 ሁልጊዜ ኃጢአታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ
እንዲድኑ እንዳንናገራቸው ይከለክሉናልና። ነገር ግን ቍጣው ወደ እነርሱ
ፈጽሞ ደርሶአል።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 2:13-16) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 2:13-16 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

3. የተሰሎንቄ አማኞች የነጳውሎስን የመልዕክት ቃል እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርገው አልተቀበሉቱም።

   ○ በነዚህ ሁለት ሃሳቦች (የመልዕክት ቃልን እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርጎ በመቀበልና እንደ ሰው ቃል አድርጎ በመቀበል) መካከል ምን ልዮነት አለ ይላሉ?

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

5. በ1ኛ ተሰሎንቄ 2:13-16 መሠረት: አንድ ሰው የእግዚአብሔር ቃል በሕይወቱ እንዲሰራ ከፈለገ ምን ማድረግ አለበት ይላሉ?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 05

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 2:17-3:5

17 እኛ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ በልብ ያይደለ ፊት ለፊት ለጥቂት ጊዜ
አጥተናችሁ፥ በብዙ ናፍቆት ፊታችሁን ለማየት እጅግ ሞከርን፤ 18 ወደ
እናንተ ልንመጣ ወደን ነበርና፥ እኔ ጳውሎስም አንድና ሁለት ጊዜ፥ ሰይጣን
ግን አዘገየን። 19 ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል
ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን?
20 እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና። 3:1 ስለዚህ ወደ ፊት እንታገሥ
ዘንድ ባልተቻለን ጊዜ፥ በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ። 2 ስለ
እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን
የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል
የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው፤ 3 በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ፥
ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና። 4 በእውነት ከእናንተ ጋር
ሳለን፥ መከራ እንቀበል ዘንድ እንዳለን አስቀድመን እንነግራችሁ ነበር፤
እንዲሁም ደግሞ ሆነ፥ ይህንም ታውቃላችሁ። 5 ስለዚህ እኔ ደግሞ ወደ

ፊት እታገሥ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ፡- ፈታኝ ምናልባት ፈትኖአቸዋል ድካማችንም ከንቱ ሆኖአል ብዬ እምነታችሁን ለማወቅ ላክሁ።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 2:17-3:5) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 2:17-3:5 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

..............................................................................................................................................................

3. ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች የነበረውን ፍቅርና ናፍቆት ሲያስቡ: ይህ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው?

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

- ○ እርስዎ ለሌሎች አማኞች ያልዎትን ፍቅርና ናፍቆት ከጳውሎስ ለተሰሎንቄ ወገኖች ከነበረው ፍቅር ጋር ሲያነጻጽሩት ምን ይላሉ? ለምን እንደዛ የሆነ ይመስልዎታል?

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

4. በቍጥር 19-20 የተጻፈው “ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን? እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና።” የሚለውን ሃሳብ እንዴት ይረዱታል?

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

..............................................................................................................................

5. *“በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ፥ ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና”* እና *“ፈታኝ ምናልባት ፈትኖአቸዋል ድካማችንም ከንቱ ሆኖአል ብዬ እምነታችሁን ለማወቅ ላክሁ”* የሚሉትን ሃሳቦች እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

..................................................................................................................................................................

..................................................................................................................................................................

..................................................................................................................................................................

..................................................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 06

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 3:6-13

6 አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ ወደ እኛ መጥቶ ስለ እምነታችሁና
ስለ ፍቅራችሁ የምስራች ብሎ በነገረን ጊዜ፥ እኛም እናያችሁ ዘንድ
እንደምንናፍቅ ታዩን ዘንድ እየናፈቃችሁ ሁልጊዜ በመልካም
እንደምታስቡን በነገረን ጊዜ፥ 7 ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በእምነታችሁ
በኩል በችግራችንና በመከራችን ሁሉ ስለ እናንተ ተጽናናን፤ 8 እናንተ
በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና። 9-10 ፊታችሁን
ልናይ በእምነታችሁም የጎደለውን ልንሞላበት ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ
እየጸለይን በአምላካችን ፊት ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥
ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ
እንችላለን? 11 አምላካችንና አባታችን ራሱ ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ
እናንተ መንገዳችንን ያቅና፤ 12-13 ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ
ሁሉ ጋር ሲመጣ፥ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት
አድርጎ ልባችሁን ያጸና ዘንድ፥ እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ
በእርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 3:6-13) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 3:6-13 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

3. ጢሞቴዎስ ስለ ተሰሎንቄ አማኞች ይዞት የመጣው መልዕክት ጳውሎስን እንዳጽናናውና አንዳስደሰተው ከንባብ ክፍሉ መረዳት ይቻላል። የጢሞቴዎስ መልዕክት ይዘት ምንድን ነው?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

○ የአንድ ክርስትያን የሕይወቱ መለኪያዎች እምነትና ፍቅር ናቸው የሚለውን አባባል ምን ያህል እውነት ነው ይላሉ? ለምን?

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

4. በቍጥር 8 “እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና።” የሚለውን የጳውሎስ አባባል እንዴት ይረዱታል?

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

○ በጌታ ጸንቶ ያልቆመ ሰው ምን ይመስላል?

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

.......................................................................................................................................................

- አንድ ክርስቲያን በጌታ ጸንቶ መቆም የሚችለው እንዴት ነው? (ተጨማሪ ማብራርያ ለማግኘት ፊልጵስዩስ ሰዎች 1:27; 4:1; 1ኛ ቆሮንቶስ 16:13; ገላትያ 5:1 ማንበብ ይቻላል)

.............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

5. በቁጥር 11-13 መሰረት፡ ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች በተመለከተ ስለ 3 ነገሮች እግዚአብሔርን ይለምናል። እነዚህ ምንና ምን ናቸው? እነዚህን የጸሎት ሃሳቦች ዛሬ እንዴት መጠቀም እንችላለን?

.............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

.............................................................................................................................................

# ጥናት ቁጥር 07

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 4:1-12

1 እንግዲህ በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ልትመላለሱ እግዚአብሔርንም
ደስ ልታሰኙ እንዴት እንደሚገባችሁ ከእኛ ዘንድ እንደ ተቀበላችሁ፥
እናንተ ደግሞ እንደምትመላለሱ፥ ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ በጌታ
በኢየሱስ እንለምናችኋለን እንመክራችሁማለን። 2 በጌታ በኢየሱስ
የትኛውን ትእዛዝ እንደ ሰጠናችሁ ታውቃላችሁና። 3 ይህ የእግዚአብሔር
ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ 4-5 ከዝሙት እንድትርቁ፥
እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ፥
ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ
እንዲያውቅ፤ 6 አስቀድመን ደግሞ እንዳልናችሁና እንደ መሰከርንላችሁ፥
ጌታ ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ
ወንድሙንም አያታልል። 7 ለርኵሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና
ጠርቶናልና። 8 እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ አይደለም፥ መንፈስ
ቅዱስን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ። 9
እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና

ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም፤
10-12 እንዲሁ በመቄዶንያ ሁሉ ላሉት ወንድሞች ሁሉ ታደርጋላችሁና።
ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ከፊት ይልቅ ልትበዙ፥ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ
ልትቀኑ፥ የራሳችሁንም ጉዳይ ልትጠነቀቁ፥ እንዳዘዝናችሁም፥ በውጭ
ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ፥ አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ
በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 4:1-12) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4:1-12 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

3. በዚህ የንባብ ክፍል መሰረት: ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞችን በአኗኗራቸው: እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደሚገባቸው ይመክራቸዋል። ይህ ለማድረግም 3 መንገዶች ያሳያቸዋል። እነዚህ መንገዶች ምንና ምን ናቸው?

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

4. *ቅድስና* የሚለውን ቃል እንዴት ይተረጉሙታል? ጳውሎስ *ቅድስና* የሚለውን ቃል ለተሰሎንቄ አማኞች እንዴት ያብራራላቸዋል?

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

- በጳውሎስና በርስዎ መካከል ቅድስናን በተመለከተ የትርጉም ልዩነት አገኙ?

.................................................................................................................................................

.................................................................................................................................................

..........................................................................................................

..........................................................................................................

5. ጳውሎስ በቁጥር 9 *“እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም”* ሲል ምን ማለቱ ነው?

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..........................................................................................................

6. በቁጥር 10-12 መሰረት፡ ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች ትጉ ሰራተኞች እንዲሆኑ ይመክራቸዋል። ጳውሎስ እንዲህ የሚልበት ምክንያት ምንድን ነው?

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..........................................................................................................

> “It is a wonderfully liberating experience when the desire to please God overtakes the desire to please ourselves, and when the love for others displaces self-love. True freedom is not freedom from responsibility to God and others in order to live for ourselves, but from ourselves in order to live for God and others” John Sttot.

# ጥናት ቁጥር 08

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-18

13 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ
እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። 14 ኢየሱስ
እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን
እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። 15 በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ
ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን
አንቀድምም፤ 16 ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ
በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ
አስቀድመው ይነሣሉ፤ 17 ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥
ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም
ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። 18 ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል
ተጽናኑ።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-18) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

○ ዛሬ በችግርና በመከራ የሚያልፉትን ወገኖች፣ የጌታን እንደገና መምጣትን እንዲያስቡ በመምከር ማጽናናት የሚቻል ይመስልዎታል? ለምን?

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

4. በቍጥር 13 “ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።” የሚል ቃል እናነባለን:: የሚያምኑ ሰዎች ሃዘን: ከሌሎች ሰዎች ሃዘን የሚለየው ለምንድን ነው?

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................

5. “በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ 17 ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤” የሚለውን ሃሳብ እንዴት ይረዱታል?

........................................................................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................................................................

........................................................................................................................................................................................................

## ጥናት ቁጥር 09

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-11

1 ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ
አያስፈልጋችሁም፤ 2 የጌታ ቀን፥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥ እንዲሁ
ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና። 3 ሰላምና ደኅንነት
ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት
ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም። 4 እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ
እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥ 5 ሁላችሁ
የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ
አይደለንም፤ 6 እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች
አናንቀላፋ። 7 የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉና፥ የሚሰክሩም በሌሊት
ይሰክራሉና፤ 8 እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር
የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤ 9
እግዚአብሔር ለቍጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ። 10 የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም
ብንሆን፥ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ ስለ እኛ ሞተ። 11

ስለዚህ እናንተ ደግሞ እንደምታደርጉ፥ እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም አንዱም ሌላውን ያንጸው።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-11) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-11 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

................................................................................................................................................

3. በዚህ የንባብ ክፍል፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፡ ለተሰሎንቄ አማኞች፡ በኋለኛው ዘመን ሊመጣ ስላለው የፍርድ ቀን ይጽፍላቸዋል። በመልዕክቱ መሰረት የተሰሎንቄ አማኞች ለፍርድ ቀን ዝግጁ መሆን የሚችሉት እንዴት ነው?

○ ዛሬ እርስዎ ለጌታ መምጣት ዝግጁ ነኝ ብለው ያስባሉ? ለምን?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

5. ጳውሎስ በቁጥር 6 የተሰሎንቄን አማኞች “እንግዲያስ **እንንቃ በመጠንም እንኑር** እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ" ብሎ ሲመክራቸው በዚሁ የንባብ ክፍል እናንባለን። መንቃትና በመጠን መኖር የጌታን መምጣት ለመጠባበቅ እንዴት ይረዳል?

# ጥናት ቁጥር 10

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ተሰሎንቄ 5:12-28

12-13 **ወንድሞች** ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም
የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፥ ስለ ሥራቸውም
በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። እርስ
በርሳችሁ በሰላም ሁኑ። 14 **ወንድሞች** ሆይ፥ እንመክራችኋለን፤ ያለ
ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤
ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ።። 15 ማንም ለሌላው በክፉ
ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፥ ነገር ግን ሁልጊዜ እርስ በርሳችሁ
ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ። 16 ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ 17-18
ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ
ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና። 19 መንፈስን አታጥፉ፤ 20-21 ትንቢትን
አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ 22 ከማናቸውም ዓይነት ክፉ
ነገር ራቁ። 23 የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤
መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ
ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። 24 የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥

እርሱም ደግሞ ያደርገዋል። 25 **ወንድሞች** ሆይ፥ ስለ እኛ ጸልዩ። 26
ከ**ወንድሞች** ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ። 27 ይህ
መልእክት ለቅዱሳን **ወንድሞች** ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አምላችኋለሁ። 28
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን፤ አሜን።

1. ያነበቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል (1ኛ ተሰሎንቄ 5:12-28) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይናገራል?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

2. በዚሁ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5:12-28 ስለ ሰው ባሕርይስ ምን ያነባሉ?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

3. በዚህ የንባብ ክፍል "ወንድሞች" የሚለው ቃል 5 ግዜ ተጽፎ

እናገኘዋለን። ይህ ለምንድን የሆነ ይመስልዎታል?

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

..........................................................................................................................................................

4. በዚሁ የንባብ ክፍል መሰረት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሰዎች ሊኖረን

የሚገባው አመለካከት እንዴት ያለ መሆን ይገባዋል?

**1. በመካከላችን በአገልግሎት የሚደክሙትን**

**2. እርስ በራሳችን**

**3. ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን (idle; undesciplined)**

**4. ድፍረት የሌላቸውን (discouraged)**

## 5. ደካሞችን

5. በ1ኛ ተሰሎንቄ 5:16-22 ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች 3 ማድረግ ያለባቸው ትእዛዞችና: 3 ማድረግ የሌለባቸው ትእዛዞች ይነግራቸዋል; እነዚህ ነገሮች ምንና ምን ናቸው?

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

6. "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።" የሚለውን ሃሳብ እንዴት ይረዱታል?

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................

........................................................................................................................................